

ምን መጠበቅ አለብኝ?

# የእኔ የጥገኝነት ማመልከቻ

> ውሳኔ በሚጠብቁበት ወቅት፣ ያለፈቃድ ወደ ሌላ አገር ለመሄድ አይውጡ።

- → አገርዎ ለእርስዎ ደህንነቱ የተጠበቀ ስላልሆነ መመለስ ካልቻሉ፣ **እዚህ ጥገኝነት መጠየቅ ይችላሉ።**
- → ጥገኝነት **ዓለም አቀፍ ጥበቃ** ተብሎም ይጠራል።
- → ብቻውን የመጣ ልጅ **(ከ18 ዓመት በታች)** ለመደገፍ ሞግዚት የሚባል ሰው ይመደብለታል።
- → ሁሉንም መረጃ ካረጋገጡ በኋላ፣ ባለሥልጣናት **ጥገኝነት እንደሚያስፈልግዎት ወይም እንደማያስፈልግዎት ይወስናሉ።**

## ምዝገባ

ባለሥልጣናት **ማመልከቻዎን ይመዘግባሉ፣ ፎቶዎን** እና **የጣት አሻራዎን** ይወስዳሉ (ከ6 ዓመት በላይ ከሆኑ) እና ሰነዶችዎን ይፈትሻሉ።

**ለጥገኝነት ማመልከትዎን የሚገልጽ ሰነድ** ይሰጥዎታል። ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያቆዩት።

ከተመዘገቡ በኋላ፣ የቃለ-መጠይቅ **ቀን**፣ **ሰዓት** እና **ቦታ** ያለው ግብዣ ይሰጥዎታል።

## ቃለ-መጠይቅን በመጠበቅ

**ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ** ይቆያሉ። በሚጠብቁበት ጊዜ፣ **ራስዎን በሥራ ይያዙ።**

የአካባቢውን ቋንቋ ይማሩ፣ አዲስ ጓደኞችን ያፍሩ፣ ስፖርት ይጫወቱ እና ጤናማ ይሁኑ።

**ለቃለ-ምልልሱ ለመዘጋጀት** እንዲረዳዎ የሕግ አማካሪን ወይም ሞግዚትዎን ይጠይቁ።



**የጥገኝነት ቃለ-ምልልስዎን እንዳያመልጥዎ!** ከታመሙ፣ ለባለሥልጣናት ያሳውቁ።

## የእርስዎ የጥገኝነት ቃለ-መጠይቅ

**አገርዎን ለቀው የወጡት ለምን እንደሆነ፣** ስለ ቤተሰብዎ፣ ስለ ቀደመው ሕይወትዎ እና ስለ ጉዞዎ ይጠየቃሉ።

ታሪክዎን ለመደገፍ **ሰነዶችን** (መታወቂያ፣ ፎቶዎች፣ ሪፖርቶች) **ይዘው ይምጡ።**

## ውሳኔው

**ከጥቂት ወራት በኋላ** ውሳኔ ይደርስዎታል።

**አዎንታዊ ከሆነ፣** በዚህ አገር መቆየት እና ወደ ይበልጥ ቋሚ መኖሪያ ቤት መሄድ ይችላሉ።

**አሉታዊ ከሆነ፣** ወደ ቤትዎ ለመመለስ እንዲችሉ ደህንነታቸው የተጠበቁ አማራጮች ይነገሩዎታል። በውሳኔው ካልተስማሙ፣ በይፋ መቃወም ይችላሉ። ይህ **ይግባኝ (Appeal)** ይባላል።

## ያስታውሱ

- ስለ መመለስ ወይም አሉታዊ ውሳኔን እንዴት መቃወም (ይግባኝ ማለት) እንደሚቻል ምክር ለማግኘት ጠበቃ ማናገር ይችላሉ።
- ቋንቋውን መናገር ካልቻሉ አስተርጓሚ ይጠይቁ።
- መኮንኑ ለሚጠይቅዎ ጥያቄዎች መመለስ ካልቻሉ፣ መናገር ይችላሉ።
- ሁሉም መኮንኖች በአክብሮት ሊይዙዎት ይገባል።
- ከመኮንኖቹ ጋር ይተባበሩ። የሚናገሩት ነገር ግልጽ ካልሆነ ምን ማለታቸው እንደሆነ እንዲያስረዱዎት ይጠይቋቸው።



Amharic

euaa
EUROPEAN UNION AGENCY FOR ASYLUM

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025